# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ህዳር 16 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ተዘጋ-ጋዜጠኞቹ ተበተኑ፤**

**በአንድ ሳምንት ብቻ ሶስት ጋዜጠኞች ከሀገር ተሰደዱ፤**

**የወያኔ ቡድን አሁንም ጦሩን ወደ ሱማሊያ ማስገባቱ ተጋለጠ፤**

ወያኔ በሚፈፅምባቸው ግፍ እና መከራ ሲሰቃዩ የነበሩ ሶስት የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞችለህይወታቸው አስጊ ሁኔታ በመፈጠሩ ሀገር ጥለው መሰደዳቸው ታወቀ::

ከቅንጅት አመራሮች ጋር እድሜ ልክ ተፈርዶበት ለ21 ወራት ታስሮ የተፈታውና በሁዋላም አውራምባ ታይምስ ብሎ በጀመረው ሳምንታዊ ጋዜጣ አዘጋጅ እና ባለቤት የሆነው ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደን ጨምሮ ሶስት ጋዜጠኞች በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ ሀገር ጥለው መጥፋታቸው ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድን በህዝብ እና በሀገር ላይ የሚሰራውን ሸፍጥ እና ደባ ሲያጋልጡ እና ይፋ ሲያደርጉ የነበሩት እነዚህ ሶስት ጋዜጠኞች በደህንነት ኃይሎች ወከባና እንግልት ሲፈጸምባቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ ለህይወታቸው አስጊ ሁኔታ በመፈጠሩ ሀገራቸውን ጥለው ለመሰደድ እንደተገደዱ ከሰጡት መግለጫ ለማወቅ ተችሎዋል::

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ለህዝቡ በሚያቀርባቸው መረጃዎች እና ጥቆማዎች የተነሳ በወያኔ የደህንነት ሃይሎች ከፍተኛ እንግልት እና ስቃይ ሲደርስበት የነበረ ከመሆኑም በተጨማሪ ከአስር በላይ የክስ ፋይሎች ተከፍተውበት በፍርድ ቤት እየተመላለሰ የሚገኝ ቢሆንም ወያኔ በቅርቡ በጀመረው ዜጎችን አፍኖ መሰወር እና መግደል ተግባር በእሱም ላይ በቅርቡ ሊፈጸምበት እንደሆነ ከሸመልስ ከማል ቢሮ የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ስለደረሰው ድንገት ከሀገር ሊወጣ እንደቻለ ታውቆዋል::

ጋዜጠኛው በሀገረ አሜሪካ ዋሽንግተን ዲ.ሲ እንደገባ ለስደት ያበቃውን ምክንያት ለተለያዩ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀንና ለፕሬስ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች እንደገለፀው ከሆነ በ1997 ዓ.ም ሀዳር የተሰኘ የነጻው ፕሬስ አካል የነበረ ሳምንታዊ ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኖ ሲሰራ በነበረበት ወቅት ከቀድሞው የቅንጅት አመራሮች ጋር ተከስሶ እድሜ ልክ ተፈርዶበት ለ21 ወራት ታስሮ በይቅርታ የወጣ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በሽብርተኝነት ስም ታፔላ ተለጥፎበት የተደረገለት ይቅርታ ተነስቶ ወደ እድሜ ልክ እስረኛነት ሊከቱት በዝግጅት ላይ መሆናቸው መረጃ ስለደረሰው አምልጦ ሀገሩን ጥሎ ለስደት እንደተዳረገ ገልፆዋል::

በየሳምንቱ ቅዳሜ ለንባብ የሚበቃው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ለአራት ዓመታት የሰራው ዳዊት ከበደ የክስ ፋይሎቹ ሲበዙበት በማኔጂንግ ኤዲተርነት ተዛውሮ እስከ ተሰደደበት ዕለት ሲሰራ የነበረ ሲሆን በተለይ ባለፉት ሁለት ተከታታይ ሳምንታት **«እውነት ይህች ሀገር የማን ናት?»** በሚል ርዕስ ባቀረባቸው መጣጥፎች የወያኔን አምባገነንነት ቁልጭ አድርጎ በማስፈሩ በወያኔ ባለስልጣናት በተለይ በእነ ሽመልስ ከማል ዘንድ ክፉኛ ቁጣን በማስከተሉ ታስሮ የእድሜ ልክ እስራት ፍርድ እንዲወሰንበት እየተዘጋጁ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮች በማጋለጣቸው ድንገት ከሀገር ወጥቶ ሊሰደድ እንደቻለ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ዳዊት ከበደ ከመሰደዱ ሁለት ቀን አስቀድሞ ሌሎች ሁለት ጋዜጠኞችም በተመሳሳይ መልኩ የወያኔ ደህንነት ኃይሎች አፍነው ሊወስዱዋቸው መሆኑ መረጃው ስለደረሳቸው ከሀገር ወጥተው መሰደዳቸው ታውቆዋል::

በብዕር ስሙ አቤ ቶኪቻው በሚል በአውራምባ ታይምስ እና በፍትህ ጋዜጣ ላይ ጠንከር ያሉ ትችቶች እና እውነት የሆኑ የህዝብ ብሶቶችን ሲያቀርብ የነበረው ጋዜጠኛ አበበ ቶላ ባለፈው ዓመት የህዝብ መነጋገሪያ የሆኑ የዕለት ተዕለት ችግሮችን የሚገልፁ አጫጭር መጣጥፎችን በመፅሀፍ መልክ አሳትሞ ለንባብ ያበቃ መሆኑም ይታወቃል::

ጋዜጠኛ አበበ ቶላ በአውራምባ ጋዜጣ ላይ ለብዙ ግዜ ሲሰራ ቆይቶ እንደገና በቅርቡ ወደ ፍትህ ጋዜጣ ተዛውሮ የህዝቡን ብሶት እና ችግር በተባ ብዕሩ እያቀረበ የነበረ ቢሆንም በደህንነቶች እና በእነ ሽመልስ ከማል ማስጠንቀቂያ ሲሰጠው የቆየ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ እንግልት ሲፈጽሙበት እንደነበረ ከሀገር ከወጣ በሁዋላ በሰጠው መግለጫ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከሀገር ወጥቶ በጎረቤት ኬንያ ውስጥ ከገባ በሁዋላም የወያኔ ደህንነት ሰራተኞች እየተከታተሉ አሁንም ከፍተኛ ማስፈራሪያ እየሰጡት ከመሆኑም በተጨማሪ አፍነው ወደ ሀገር ቤት ሊመልሱት እየሞከሩ መሆኑና ቀንና ሌሊት ሳይል ተደብቆ እንደሚገኝም ከገለፃው ለመረዳት ተችሎዋል::

ሌላው በቅርቡ ለንባብ የበቃው እና የአንድነት ልሳን የሆነው የፍኖተ ነጻነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ባልደረባ ጋዜጠኛ ሲሳይ የወያኔ ከፍተኛ የደህንነት ባለስልጣናት ጭምር ስራውን እንዲያቆም አለበለዚያ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል በተደጋጋሚ ግዜ ማስጠንቀቂያ ከመስጠታቸውም በላይ እቢሮው ድረስ እየገቡ ሲያስፈራሩት እንደነበረና በመጨረሻ ግን ህይወቱን ሊያጣ እንደሚችል ስለተነገረው ድንገት ሀገር ጥሎ ሊሰደድ እንደቻለ ታውቆዋል::

ችግሮችን ተጋፍጦ በሀገር ውስጥ እየሰራ የሚገኝ ጠንካራ ጋዜጠኛ ተብሎ በቅርቡ የዓለም አቀፍ ሽልማት ተሸላሚ የሆነው ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በተደጋጋሚ ግዜ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣኖች አባል ሆኖ አብሮዋቸው እንዲሰራ ቢጠየቁትም አልሰራም አባልም አልሆንም በማለቱ ብቻ በየቀኑ ከፍተኛ እንግልት እና ወከባ ሲደርስበት የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ቅርበት ያላቸው ወገኖች በተለይ ትግሬ ሆነህ እንዴት መልሰህ እኛን ታጠቃለህ? በማለት ተራና በወረደ ማሳመኛ ቃላት ሊቀይሩት ቢሞክሩም እኔ ኢትዮጵያዊ እንጂ ጎጠኛ አይደለሁም በማለት ቆራጥ መልስ በመስቱ የተበሳጩት ባለስልጣናቱ ልዩ የደህንነት ኃይሎች ክትትል እንዲያደርጉበት እና እያንገላቱ እንዲያሰቃዩት መደረጉን ቅርበት ካላቸው ሰዎች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

አቤ ቶኪቻው በበኩሉ በቢሮውና ከቢሮው ውጭ የደህንነት ኃይሎች እየተከታተሉት መጻፉን እንዲያቆምና የወያኔ አባል ሆኖ እንዲቀጥል ብዙ ጥረት ቢያደርጉም አልሳካ ሲላቸው እንደሚገድሉት በግልጽ እንደተነገረው በይፋ ገልፆዋል::

ጋዜጠኞቹ ከሀገር ከተሰደዱ በሁዋላ በተለይ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ወደ አሜሪካ ከገባ በሁዋላ የሰጠውን መግለጫ ተከትሎ የዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት (ሲፒጂ) እና ሂዩማን ራይትስ ዎች የተሰኙት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ባወጡት መግለጫ የጋዜጠኞቹ መሰደድ በኢትዮጵያ ውስጥ የፕሬስ ሁኔታ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያሳይ ነው ብለዋል::

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ከሀገር ከወጣ በሁዋላ የብሮድ ካስት ባለስልጣን የሆነው መስሪያ ቤት እና የፍትህ ሚኒስትር በየፊናቸው በብስጭት እና በንዴት መግለጫ ያወጡ ሲሆን በዚሁ በሰጡት መግለጫ ላይ እንዳሉት ከሆነ ይቅርታው ይነሳል የሚባለው ፍጹም የተሳሳተ ነው ብለዋል::በተለይ በበረከት ስምዖን የሚመራውና በሽመልስ ከማል ጋሻ ጃግሬነት የሚንቀሳቀሰው የብሮድ ካስት መስሪያ ቤት በተደጋጋሚ ካሰራጨው ዜና ለመረዳት እንደተቻለው ወያኔ ባለስልጣናት ገመናቸው በመጋለጡ እጅግ እንደተበሳጩ በግልጽ ሚያሳይ ነው ሲሉም ምሁራኖች ይገልጻሉ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ከሀገር ወጥቶ መሰደዱን ተከትሎ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ከዚህ በሁዋላ ህትመት ማቆሙ ታወቀ::ከ15 ያላነሱ ጋዜጠኞችንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በስሩ ይዞ የነበረው የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ከህዳር 9 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከህትመት ውጪ መሆኑ ከዝግጅት ክፍሉ ሰራተኞች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

ለህዝቡ መረጃን በመስጠት ግንባር ቀደም ከሆኑት የፕሬስ ውጤት ዋነኛዋ ተጠቃሽ የነበረችው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ለአራት ዓመታት ያህል ግዜ በየሳምንቱ ቅዳሜ ስታሰራጭ የነበረ ቢሆንም የጋዜጣው ባለቤት ዳዊት ከተሰደደ በሁዋላ ከህትመት ውጭ እንድትሆን መደረጉዋ ታውቆዋል::

ዛሬ በሀገሪቱ ስራ አጥ ዜጎች በሚሊዮን እየተቆጠሩ ባለበት በዚህ ግዜ ለፍተው ጥረው ግረው ለህዝቡ መረጃን በማቀበል ብሎም በሚያገኙዋት የዕለት ጉርስ እየተፍጨረጨሩ በነበሩበት ወቅት ጋዜጣዋ እንድትዘጋ መደረጉ በሀገሪቱ እጅግ የከፋና የጨለመ አስተሳሰብ የሰፈረባቸው ገዥዎች

እየፈጸሙ ያሉት አሳፋሪ ድርጊት የሚጋለጥበት ግዜ ነው ሲሉ እነዚሁ የጋዜጣዋ ዝግጅት ክፍል ባልደረቦች በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

በቅርቡ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ እና የፍትህ ጋዜጣ አምደኛ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከስሰው በቃሊቲ እስር ቤት ታስረው ይገኛሉ።

በሌላ ዜና ከሶስት ዓመት በፊት ከኢትዮጵያ ህዝብ እውቅና ውጭ ወደ ሱማሊያ ገብቶ ከፍተኛ ኪሳራ ተከናንቦ የተመለሰው የወያኔ ጦር በድጋሚ ሰሞኑን ወደ ሱማሊያ መግባቱ ተጋለጠ።

በወርሀ ግንቦት 2003 ዓ.ም ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ የተመመው የወያኔ ጦር በአሁኑ ሰዓት አንድ ብርጌድ ጦር ወደ ሱማሊያ ዘልቆ መግባቱን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

እንደ መከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ከሆነ የወያኔ ጦር ባለፈው ሳምንት ወደ ሱማሊያ አንድ ብርጌድ ጦር በከባድ መሳሪያ ታግዞ ያስገባ ይሁን እንጂ ባለፈው ዓመት ከግንቦት ወር ጀምሮ በተነጣይ ሻምበሎች ቅኝት እና ጥበቃ ሲያደርግ እንደነበረ ገልፀዋል።

ሰሞኑን ግን የኬንያ ጦር ከአልሻባብ ጋር የጀመረውን ውጊያ መቋቋቋም ስለተሳነው የወያኔ ሰራዊት እገዛ እንዲያደርግለት የኬንያ ባለስልጣናት በመማጸናቸውና ምስጢራዊ ስምምነት በመፈጸማቸው የተነሳ አንድ ብርጌድ ጦር ወደ ሱማሊያ ዘልቆ እንዲገባ ሲደረግ ታንክ እና መድፍን ጨምሮ ሌሎች ከባድ መሳሪያዎችን እንደታጠቀም ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

ይህንኑ የወያኔ ጦር ወደ ሱማሊያ ውስጥ ዘልቆ መግባቱን ተከትሎ የተለያዩ የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ጭምር እየዘገቡ ሲሆን ወያኔ በበኩሉ እያስተባበለ ይገኛል።የወያኔ ጦር የሱማሊያን ድንበር አቋርጦ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ አንድ ንዑስ ጣቢያ ላይ ግዜያዊ ማረፊያ ካምፕ የመሰረተ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በተለይ በኬንያ አቅጣጫ አልሻባብ ጥቃት እየሰነዘረ ባለበት መስመር ላይ የከባድ መሳሪያ ድብደባ ማድረግ መጀመሩንም የምንጮቹ ጥቆማ ያብራራል።ይህንኑ የከባድ መሳሪያ ድብደባ ተከትሎ ደግሞ ሶስት የወያኔ የጦር ጄቶች የአልቃይዳ ይዞታዎች ናቸው የተባሉት ቦታዎች ላይ ድብደባ እየፈጸሙ ሲሆን በድብደባው ከብቶች እና ሰዎችም ሞተው መታየታቸው እየተገለፀ ይገኛል።

በአሁኑ ሰዓት ወደ ሱማሊያ ከገባው አንድ ብርጌድ ጦር በተጨማሪ ሌሎች ሁለት ብርጌዶች ፌርፌር እና ቀላፎ በተባሉ ቦታዎች ላይ ሰፍረው በተጠንቀቅ የሚገኙ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በበላይነት ከሐረር ሆኖ የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ሜ/ጄ/ል መብርሀቱ የተባለው የበረሀ ታጋይ እየመራው እንደሆነም ምንጮቹ ገልፀዋል።

ኬንያ ላለፉት አምስት ሳምንታት ከዓለም አቀፉ አሸባሪ ከሆነው አልቃይዳ ጋር ግንኙነት አለው የተባለው አልሻባብ ጋር ከፍተኛ ውጊያ ስታደርግ ብትሰነብትም ከአቅሙዋ በላይ በመሆኑ በምስራቅ አፍሪካ ሀገራት እና በገልፍ ሰላጤ ያሉ ሀገሮች በገንዘብ እና በፖለቲካ እገዛ እንዲያደርጉላት ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ያደረገች ሲሆን በተለይ ኢትዮጵያ በጦር ኃይል እንድታግዛት በምስጢር

ዲፕሎማቶችዋን አዲስ አበባ ልካ የነበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወያኔ ድንበር ላይ ሰፍሮ ከነበረው ግዙፍ ጦር መሀከል አንድ ብርጌድ ማስጋባቱን ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል፡፡

እንደ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ የወያኔ ጦር ጉሪል የተባለውን የሱማሊያ ወረዳ አልፎ ወደ 90 ኪሎ ሜትር ዘልቆ ከመግባቱም በተጨማሪ በአቅራቢያ የሚገኙ የሱማሌ ተወላጆችን ከአልሻባብ ጋር ግንኙነት አላችሁ በማለት ለቀናት ማሰር መጀመሩንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የኬንያ ጦር በምድር ኃይሉ ቢሞክርም አልሳካ ሲለው የባህር ኃይሉን ጭምር ወደ አውደ ውጊያው ቢያስገባም በአልቃይዳ ጦር ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት እና መቁዋቁዋም ስላቃተው የድረሱልኝ ጥሪ በማሰማቱ ዜጎችን የጥይት ማብረጃ ለማድረግ ወያኔ በለመደው መንገድ ከኢትዮጵያ ህዝብ እውቅና እና ፍቃድ ውጭ ጦሩን ማዝመቱ እጅግ አስገራሚ ነው ሲሉም የፖለቲካ ተንታኞች ይተቻሉ፡፡

የኢትዮጵያ ጦር ከፍተኛ ኪሳራ ደርሶበት ከሱማሊያ ለቅቆ ከወጣበት ግዜ ጀምሮ የተለያዩ ሀገራት ወታደሮች በሰላም አስከባሪነት ስም በሱማሊያ ሰፍሮ የሚገኝ ቢሆንም እስከ አሁን በሀገሪቱ ሰላም ሊሰፍን ያልቻለው የሽግግር መንግስቱ ባለስልጣናት እርስ በርስ ስምምነት በማጣታቸው መሆኑም እየተነገረ ይገኛል፡፡

በተለይ በሻዕቢያና በወያኔ መሀከል በሚደረገው የርስ በርስ ሽኩቻ አልቃይዳን የኢሳያስ አፈወርቂ ቡድን በመሳሪያና በቁሳቁስ እንዲሁም በየወሩ 80 ሺህ ዶላር (1.3 ሚሊዮን ብር) ድጋፍ በማድረግ እያገዘ ሲገኝ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ደግሞ ገንዘብ በመደጎምና ጦር በመስጠት የሽግግር መንግስቱ በአንድ እግሩ እንዲቆም እየጣረ ቢሆንም እስከ አሁን የታሰበው ሳይሆን ቀርቶዋል፡፡

ከሁሉም በላይ የሽግግር መንግስቱ ውስጥ ተመርጠው የሚመጡ የሱማሊያ ባለስልጣናትን በእነ መለስ ፍቃድ እሚመሩ ለማድረግ በሚጥሩበት ወቅት የእርስ በርሱ ሽኩቻ እንደሚፋፋምና እስከ አሁን ድረስም ይህ ችግር ሊቀረፍ ባለመቻሉ በሱማሊያ የሽግግር መንግስት ባለስልጣናት ዘንድ ክፍተቱ እየሰፋና እየገዘፈ በመምጣቱ ሰላም ሊወርድ እንዳልቻለ የሚናገሩት የፖለቲካ ተንታኞች አሁንም በመሳሪያና በጦር ጋጋታ በሱማሊያ የሚመጣ አንዳችም ሰላም የለም ሲሉ ይመክራሉ፡፡

በምስራቅ ኢትዮጵያ በኩል ወደ ሱማሊያ ጦሩን ያስገባው የወያኔ ቡድን በሰሜን ኢትዮጵያ ደግሞ ከሻእቢያ ጋር መጠነኛ ግጭት ሳይፈጠርበት እንዳልቀረ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋለጠ፡፡

ሰሞኑን ከመከላከያ ዋና መመሪያ ሾልኮ የወጣው ጥቆማ እንዳስረዳው ከሆነ በአሰብ መስመር ቡሬ አቅራቢያ ሰፍሮ የሚገኘው የሻእቢያ ጦር ጋር መጠነኛ የተባለ የተኩስ ልውውጥ መደረጉን ተከትሎ የወያኔ የጦር አዛዦች በያሉበት ዝግጅት እንዲያደርጉ ከሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ መተላለፉ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

የዋና መምሪያው መቀመጫ መቀሌ የሆነው የሰሜን እዝ ዋና አዛዥ ሌ/ጄ/ል ሳዓረ መኮንን እና ዋና መቀመጫው ሽሬ እንዳስላሴ የሆነው የማዕከላዊ እዝ ዋና አዛዥ ሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ

ሰሞኑን የጦር ክፍላቸው ለውጊያ ዝግጁ እንዲሆንና በተጠንቀቅ እንዲቆም ማዘዛቸውን ከመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ለህዝብ ሳይሆን ለግላቸው......ለሀገር ሳይሆን ለጎጣቸው......ለልማት ሳይሆን ለጥፋት .....የሚሽቀዳደሙት የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂና የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የየሀገሮቹ ህዝቦች የርሀብ ነጋሪት እየጎሰመ መጣሁ መጣሁ እያለ በሚልበት እና የኑሮ ውድነት ጠፍሮ በያዛቸው በዚህ ወቅት የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም ሲሉ ብቻ የሰው ልጆችን ለማጫረስ የውጊያ ዝግጅት እያደረጉ መገኘታቸውን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

የወያኔ የጦር ጄኔራሎች ከአንድ ወር ወዲህ በሀገሪቱ ያሉ የጦር ክፍሎች በሙሉ የውጊያ ልምምድ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ በተለይ የመሳሪያና ተሽከርካሪ ጥገና እንዲደረግ በማዘዛቸው በሁሉም ካምፖች ውስጥ ዝግጅቱ እየተጡዋጡዋፈ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ ከውጭ ሀገር ዩክሬን ተገዝተው የመጡትን ታንኮች እና ሌሎች ዘመናዊና አዳዲስ ከባድ የጦር መሳሪያዎች በየጦሩ ክፍሎች የተበተኑ ሲሆን በመሀል ሀገር ውስጥም በምስጢር እንዲቀመጡ የተደረጉ መኖሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ዘገባ ያስረዳል፡፡

አንድ የቀድሞ ከፍተኛ የጦር መኮንን ስለ ሁኔታው ሲገልጹ በአሁኑ ሰዓት ሁለቱ ቡድኖች ማለትም ሻዕቢያ እና ወያኔ ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ ስለደረሰባቸው ብቻ ይህችን ለመሸፈን ሲሉ መጠነኛ ግጭት ለመፍጠር የሚሞክሩ ከመሆኑ በላይ የታክቲክ ግጭት እንጂ እውነተኛ አለመሆኑን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱን ሲያስረዱ ደግሞ ጦሩ በአንድ ወገን የበላይነት በመመራቱ ውስጡ እየታመመ ከመሆኑም በላይ በሀገሪቱ ህዝቦች ላይ የሚደርሰውን በደልና ግፍ ስለሚያውቅም በተለይ በርሀብ እየሞተ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ያለው የህዝብ ልጅ በመሆኑ በስርዓቱ ላይ አንድ ቀን ችግር ሊፈጥር ይችላል በሚል ስጋት እና ፍርሀት ብቻ የሻዕቢያ ጦር ሊወጋህ ነው እያሉ እራሱን ወጥሮ እንዲኖር ያደረጉበት ስልት ነው ሲሉም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በመጨረሻም በደቡብ ክልል በዳውሮ ዞን በዋካ ከተማ በህዝብ ላይ የሚደርሰውን ሰቆቃና ግፍ በመቃወም ሲገልጽ የነበረው ወጣት መምህር የኔሰው ገብሬ እራሱን አቃጥሎ ከሞተ በሁዋላ በዞኑ ከፍተኛ ቁጣ መቀስቀሱ ተገለፀ፡፡

የመምህር የኔሰው ሞትን ተከትሎ ወጣቱ በህብረት በመሆን በየአቅራቢያው በሚገኙ ሹማምንቶች ላይ ተቃውሞ ከማሰማቱም በተጨማሪ ይህች ሀገር የማናት በማለት በመዝሙር መልክ ተቃውሞ እያሰሙ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ቁጥራቸው ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ የመጣው ተቃውሞ አቅራቢ ወጣቶች ታፍሰው ለእስር የተዳረጉ ቢሆንም ህዝቡ አሁንስ በዛ በማለት በቆንጨራና በዱላ በማስፈራራት በሙሉ ያስፈታቸው ሲሆን የወያኔ ባለስልጣኖችም በመፍራት አንድ ሻለቃ የፌዴራል ፖሊስ አካባቢውን እንዲቆጣጠረው ማስመጣታቸው ታውቆዋል፡፡

መልካም አስተዳደር የለም......ህዝብ ፍትህ አላገኘም.......ሰርቶ የመኖር መብቱ አልተከበረለትም......በርሀብ እና በኑሮ ውድነት ህዝቡ እያለቀ ወያኔ ዝምታን መርጦዋል......የሚሉና ሌሎችንም ተቃውሞ ሲያሰማ ምላሽ ያላገኘው ወጣት መምህሩ በብስጭት እራሱን ነዳጅ አርከፍክፎ ያቃጠለ ቢሆንም የወያኔ አፈድፋጅ የሆነው ሳምሶን ማሞ የተባለው የኢትዮ ቻናል ጋዜጣ አዘጋጅ መምህር የኔሰው የሞተው የአእምሮ ህመምተኛ ስለሆነ ነው በማለት ለኢትዮጵያ ህዝብ ሲል የከፈለውን መስዋዕትነት ሲሳለቅበት መሰንበቱ ታውቆዋል፡፡

ሳምሶን ማሞ የተባለው ግለሰብ በሚያሳትመው ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ ላይ ያሰፈረውን ዘገባ የተመለከቱ የፖለቲካ አዋቂዎች ወጣቱ ለህዝብ ሲል የከፈለውን መስዋዕትነት እንደ ርካሽ ተግባር ቆጥሮ ማጣጣል ነገ የታሪክ ተጠያቂነትን እንደሚያመጣ ካለማወቅ የመነጨ ነው በማለት የግለሰቡን ትችት ውድቅ አድርገውታል፡፡

ዛሬ መላው የሀገሪቱ ህዝቦች በወያኔ አፋኝ የፖለቲካ ስርዓት መላወሻ መተንፈሻ ባጡበት በዚህ ግዜ እራሱን መስዋዕት አድርጎ ለሌሎች አርአያ ሆኖ ትግሉ እንዲቀጣጠል ያደረገ ጀግናን ሊወደስ እና ሊሞገስ ሲገባ እንደ ተራ ድርጊት ለማጣጣል መሞከሩ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ የወያኔ ባለስልጣናትም ህዝብ እንደተንገሸገሸባቸው ከበቂ በላይ እያወቁ ለማስመሰል ብቻ እንቶ ፈንቶ ምላሽ መስጠታቸው አስገራሚ ነው ሲሉ እነዚሁ የፖለቲካ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡